# ስለ አፍ.... ስለ ቅልልቦሽ..... ከአምስቱ ጠጠሮች ስለ ሶስቱ

Elssa Mulugeta

ያው ሁሌ Adam Reta ከሚስላቸው ገፀ ባህርያት ጋር ተዛምጄ ቤተሰብ ሆኜ ቁጭ የምለው ነገር አለ (እኔ እኮ እንኳን ከሠዎቹ ከህማማት እና በገናው የብርሃኑ ፍየል ሳይቀር በፍቅር የወደቅሁ ሰው ነኝ) .....እናም ይሄ አመሌ አፍ በተሰኘው አዲሱ መፅሃፉም አልተወኝም ......ወጥቼ በገባሁ ተኝቼ በነቃሁ ቁጥር ከመፅሃፍት መካከል አፍን ሳይ የሚሰሙኝ የሚመስሉኝ የምጠይቃቸው ወ ዘ ተ

**ጠጠር1 ጌርሳሞት**

"መላእክት ከንፈሯ ላይ ቅልልቦሽ ይጫወታሉ " የተባለለትን የጌርሳሞት ከንፈር ውበት ለተማሪዎቼ ለመተረክ የነበረኝ ብቸኛ አማራጭ ቆ*ጥን ያህል አብይ ብልት የግንቦት ልደታ የብረት ምጣድ ጥብስ ላይ ባለ ተራ ስጋ ቀይሮ መንገር ነበር ...... እኒህ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎቼ አድገው መፅሃፉን ሲያነቡት ምን ይሉ ይሆን?

**ጠጠር2 ገለታ**

በርግጥ በቅልልቦሽ ጨዋታ ከመሬት የቀለብናቸውን ጠጠሮች ማስፈር ወደ ሚባል ደረጃ ስንደርስ በአውራ ጣታችን እና ጠቋሚ ጣታችን መሃል አውራ ጣታችንን በማዛነፍ በምንሰራው ረባዳ ቦታ ላይ ጠጠሮቹን አስቀምጠን ወደ አየር ስንበትን ወደ አየር የበተንናቸውንም በአይበሉባችን ልናሰፍር ስንጥር አይበሉባችንን ስተው ወደ መሬት እንደሚወድቁ አንዳንድ ጠጠሮች ቢሆንም ገለታ እስከ ዲምፐሉ እስከ እንጉርጉሮው Micky ን ስለሚመስለኝ ይሆን አብዝቼ የምንሰፈሰፍለት? ....... ትዝ ባለኝ ቁጥር "ገለታ ለምን ለምን ሞተ"ን በዜማ የምለው????

**ጠጠር3 ባካፋ የመዝጌ ልጅ** ❤️

ከምንም ነገር የበለጠ ምግብን የሚወደው ባካፋ ...... ብዙ ሰው መውደቂያው አብዝቶ በሚወደው ነገር ነውና ኬንያ ሄዶ የዝንጀሮ ስጋ በላ (አውቆ ባይሆን) እንሆ በጠናም ታመመ ...... ታዲያ እኔ ይመስለኛል ባካፋ የበለው የዝንጀሮ ስጋ እርም የሆነበት ልክ እንደ ዘመድ ስጋ ......... የባካፋ የአይን ፍቅር የነበረችው ጌርሳሞት አባት ኮላሴ ይሄን ህብረተሰብ አይቶም ነርቶም ቢያቅተው ወይ ዘር ከልጓም ስቦት ....... ብሄረሰብ < ከብሄረባቡን ....... አይነት ስሌት ውስጥ ገብቶ ? ብቻ እኔኛ የሆነ ቀን ድንገት ተነስቶ ልብሱን እየቀደደ እየተወራጨ ወደ ሰበታ ጋራ ወደ መናገሻ የገደሉን ህልም ተከትሎ ነጉዷል ....

እና ማን ያውቃል ኮላሴ መሪ የሆነለት የዝንጀሮ መንጋ መናገሻን ለቆ ከሄደ በሁዋላ እግሩና ጭራው መንጠልጠል መዝለሉ ኬንያ አድርሶት እንደሆነ ......

ማን ያውቃል የዝንጀሮ መንጋ ለማደን መሣሪያውን ታጥቆ ጫካ ጫካውን የሚሮጥ ኬንያዊ ፊት አንድ ገመሬ ዝንጀሮ በኩራት ቆሞ "እኔን ገለህ በሬሳዬ ላይ ተራምደህ ነው መንጋዬን የምትነካው " በሚል ስሜት ቆሞ እንደነበር ......

ማን ያውቃል ያ አዳኝ "ምን እንዲህ ያስፈጥጠዋል " በሚል ደመ ነፍስ የመሳሪያውን ቃታ ስቦ ከፊቱ የቆመውን ዝንጀሮ ዘርሮት እንደሆነ ........

ማን ያውቃል ሬሳውን በወሳንሳ ከአንድ ምግብ ቤት ጀርባ ወስደው አርደው በልተውት እንደሆነ ...... ማን ያውቃል ኮላሴ የጌርሳሞት አባት በሳህን ተከሽኖ ባካፉ ፊት ቀርቦ ከሆነ...... እና ይሄ እርም አይደል? ????.......

ብቻ ምን አውቃለሁ እንዲህ እንዲህ ይመስለኛል........